# *ከአውሮፓ የኢሕአፓ አህጉራዊ ፓርቲ ኮሚቴ የተሰጠ ጋዜጣዊ መግለጫ*

በአውሮፓ አህጉር የኢሕአፓ ፓርቲ አባላት ልዩ ጉባኤ በጥር 10 ና 11 ቀን 2000 ዓ.ም. ተደርጎ በተሳካ ሁናቴ ተጠናቀቀ። ይህ ከተለያዩ ሀገራዊ ፓርቲ ኮሚቴ የተወከሉ በርካታ አባላቱ በተገኙበት የተካሄደው ልዩ ጉባኤ በየሀገሩ ስላሉት ተቋማቱ፤ ስለሚገኙበት አጠቃላይ ሁናቴ በተለይም ደግሞ ባለፈው አመት መጨረሻ በተደረገው የኢሕአፓ አስቸኳይ ጉባኤ ወቅት ጥቂቶች ጉባኤውን ረግጠው ከወጡ በኋላ ስለተከሰተው አሳዛኝ ሁኔታ በጥልቀት ተወያይቷል። በርካታ ግንዛቤውችንም ወስዷል። የደረሱ ጉዳቶች የሚታረሙበት፤ የተዛቡ አሰራሮች የሚስተካከሉበት፤ ተጠናክሮ በሚገኝበት ይበልጥ የሚዳብርበት ውሳኔዎችንም አስተላልፏል። አስፈላጊ መመሪያዎችን ሰጥቷል። በአውሮፓ ሀገራት ደጋፊ ኮሚቴዎችን ማደራጀትና ማጠናከር ከድርጅቱ ጋር የሚኖራቸውንም ትስስር በአዲስ መንፈስ ለማዳበር እንዲቻልም መመሪያዎች እንዲወርዱ ወስኗል።

ቀደም ብሎ በኢሕአፓ የጀርመን ደጋፊ ኮሚቴ የተዘጋጀው የደጋፊ ኮሚቴ አባላት ስብሰባ በርካታው አባላቱ በተገኙበት በእንግድነት በተጋበዙት የከፍተኛ አመራር አባላት ስለ ወቅታዊ የኢትዮጵያ ሁናቴና ስለ ኢሕአፓ በተደረገላቸው ሰፊ ገለጻና ማብራሪያ ተመርኩዘው ለተካሄደው ውይይትና ለተወሰደው ውሳኔ ጉባዔው ከፍተኛ አድናቆቱን ገልጿል። የደጋፊ ኮሚቴው ልሳን የሆነው የአደራ መጽሔት ቅጽ 2 ታትሞ ለንባብ መቅረቡን በማየት ያለውን ምስጋና በማቅረብ ወደፊት ሕትመቱ ሳይቋረጥ እንደሚቀጥል ያለውን ተስፋና ምኞትም አስተላልፏል። ደጋፊ ኮሚቴው ወደፊት በሚያደርጋቸው ድርጅታዊ እንቅስቃሴዎች፤ አባላቱ ለኢሕአፓ እያደረጉ ያሉትን የፖለቲካና የገንዘብ ድጋፍ እንዲቀጥሉበት አደራውን ሲያስተላልፍ ለሚያስፈልጋቸው ትብብርም ዝግጁነቱን ካሁን በፊት እንዳደረገው ሁሉ ወደፊትም እንደሚቀጥልበት ጉባኤው አረጋግጧል።

በወቅታዊ የኢትዮጵያ ፖለቲካ፤ ማህበራዊና ኤኮኖሚያዊ ሁናቴ ላይ በመንተራስ በተደረገው የጠለቀ ውይይትም ሕዝባችን በአምባገነኑና አሸባሪው የመለስ አገዛዝ እየደረሰበት ያለውን ስቃይና በደል፤ በቀላሉ ሊወገድ በሚችሉ በሽታዎች



EPRP
P.O.Box 73337
Washington D.C. 20056
U.S.A
Tel. : (202) 291-4217
Fax : (202) 291-7645

EPRP
BP 22
Bois Colombes 92270
France

E-mail ESPIC@aol.com Website: http://www.EPRP.com

መጠቃቱ፤ የሥራ አጥ መበራከት፤ የፍትህ ጉድለት፤ የሰላም፣ ማህበራዊ መረጋጋትና የመልካም አስተዳደር እጦት አሁንም ገና ያልተፈቱ የሕዝባችን የፖለቲካ ጥያቄዎች መሆናቸውን ተገንዝቧል። በተለይም ደግሞ በመጠነ ሰፊ ፕሮፓጋንዳ ታጅቦ እየተነዛ ያለው የሰላም መገኘትና የኤኮኖሚ እድገት የሕዝባችንን የኑሮ ሁናቴ ቅንጣትም ታህል ፈቅ እንዳላረገለት እንዲያውም መሰረታዊ የሆኑ ለኑሮው የሚያስፈልጉት እቃዎች ዋጋ በየጊዜው የሚያሳየው ንረት የበለጠ የኑሮ ጣሩን አባብሰውበታል። ለዚህ ሁሉ ችግር ተጠያቂ የሆነው የወያኔ አገዛዝና ሥርዓቱ በቅድሚያ መወገድ ወደ ተሻለና ዴሞክራሲያው ሥርዓት ለመሸጋገር መሰረት መሆኑን ዛሬም አጽንዖት ሰጥቶ የተመለከተው ሲሆን፤ ይህንንም ስኬታማ ለማድረግ ኢሕአፓ በተለያዩ ዘርፎች የሚያደርጋቸውን ትግሎች ይበልጥ ለማጠናከር በአዲስ መንፈስ መዘጋጀቱን ጉባኤው አረጋግጧል።

በሻዕቢያና በወያኔ አገዛዝ መካከል በተደረገው አስከፊ ጦርነት ሕይወታቸውን ያጡ፤ ብዙዎች ደግሞ የደረሰባቸው የአካል ሥብራትና ጉዳት ያስከተለባቸው የመንፈስ ቁስልና ሀዘን በአግባቡ ሳያጋግም፤ ለችግሩም ተገቢው መፍትሄ ሳይገኝ በሶማሌ የውስጥ ጉዳይ እያደረገ ባለው የጦር ጣልቃ ገብነት ያስከተለው ሰብዓዊና ማህበራዊ ቀውስ ያሳዘነው መሆኑን ገልጿል። ከዚህ አንጻር በሰሜኑ የሀገራችን አካባቢ በመካሄድ ላይ ያለው የጦር ግጭት በምንም አይነት የሀገር አንድነትን ጥበቃ መሰረት ያደረገ ባለመሆኑ እንደሌሎች ችግሮች ሁሉ ሰላማዊና ዴሞክራሲያዊ መፍትሄ እንዲያገኝ ጥሪውን ያቀርባል። በዓለም አቀፍ ማህበረሰቡም በኩል ለመለስ አገዛዝ የሚደረገው የፖለቲካ፤ የገንዘብና የወታደራዊ ድጋፍ ሁኔታውን አባብሶ የበለጠ ጉዳት ከማድረሱ በፊት ሁሉም ሀገር ወዳድ ኢትዮጵያዊ ሀገራችንን ለማዳንና ሕዝባችንን ለመታደግ ትግሉን በተጠናከረ መልክ እንዲቀጥሉ ጥሪውን አስተላልፏል። የዓለም አቀፍ ሰላም ወዳድ ሕዝብም የኢትዮጵያን ሕዝብ ነጻነቱን ለመጎናጸፍ የሚያደርገውን ትግል በመደገፍ ከጎኑ እንዲቆሙ ጥሪውን አቅርቧል።

በተለያዩ የሀገራችን ክፍሎች በሚገኙ ግልጽና ስውር ማጎሪያ ቤቶች የሚገኙ የፖለቲካ እስረኞች በሙሉ ያለምንም ቅድመ ሁኔታ ተፈተው ከቅርብ ቤተሰቦቻቸው ጋር ተቀላቅለው ሰላማዊ ኑሯቸውን የሚቀጥሉበት ሁኔታ እንዲገኝ ለማድረግ ኢሕአፓ የሚያደረገውን ትግል በሙሉ ልብ እንደሚደግፍም አረጋግጧል። ደብዛቸው የጠፋ ዜጎቻችን ሁናቴ ግልጽ እንዲሆንም ሁሉም ሀገር ወዳድ የበኩሉን አስተዋጽኦ እንዲያበረክት ሀገራዊ ጥሪውን አስተላልፏል።



EPRP
P.O.Box 73337
Washington D.C. 20056
U.S.A
Tel. : (202) 291-4217
Fax : (202) 291-7645

EPRP
BP 22
Bois Colombes 92270
France

E-mail ESPIC@aol.com Website: http://www.EPRP.com

ኢ.ሕ.አ.ፓ የተመሰረተበትን 36ኛ አመት በደመቀ ሁኔታ ለማክበር ዝግጅቱ ከአሁኑ እንዲጀመር፤ ይህንን ዕውን ለማረግም ሁሉም አባላት ተግተው እንዲንቀሳቀሱ ጉባኤው ተስማምቷል።

በመጨረሻም የድርጅቱን አህጉራዊ እንቅስቃሴ ተግባራዊ ለማረግ ለሚቀጥሉት የሥራ ዓመታት በኃላፊነት የሚያገለግሉ የዞናል ኮሚቴ አባላትን ከመረጠ በኋላ ተሰብሳቢው "የትግሉ ነው ሕይወቴ" የሚለውን ታሪካዊ መዝሙር በደመቀ ሁኔታ በመዘመር ጉባዔውን አጠናቋል።

የኢትዮጵያ ህዝብ ትግል ያቸንፋል!!



EPRP
P.O.Box 73337
Washington D.C. 20056
U.S.A
Tel. : (202) 291-4217
Fax : (202) 291-7645

EPRP
BP 22
Bois Colombes 92270
France

E-mail ESPIC@aol.com Website: http://www.EPRP.com